# የዶክተር ብርሃኑ ነጋ እና የእነ አቶ መርሻ ዮሴፍ ማንነት በተግባር ሲፈተን

_____ ከኃይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

ቅንጅት እና ሕብረት በምርጫ 97 ከኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኙት ድጋፍ ለድል ቀርቦ የነበረውን ሁኔታ ጥቂት ከሃዲ ሰዎች ወደ ኋላ ለመጎተት በሰሩት ድብቅ ሴራ ተሰናክሎ፣ ያለቀለትና ሞቶ የነበረውን ወያኔን ነፍስ አድን ሆነው በደም ስሩ የደረሱለት የውስጥና የውጭ መልዕክተኞች ተግባር ይዋል ይደር እንጂ መሰሪ ዓላማቸው ተጋልጦ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነታቸውን አውቆ ዞር በሉ እያላቸው መሆኑን እየተመለከትን ነው::

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቀድሞውንም ወደ ቅንጀት ሲገባ ተልዕኮ ይዞ እንጂ ወያኔን ለመጣል እንዳልሆነ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች እና እራሱም በተግባርም እያሳየን በመሆኑ "የአራዳነቱ" ዘመን እንዳለፈበት ሊያውቀው ይገባል:: ዶክተር ብርሃኑ ለድብቅ ዓላማው ያሰለፋቸው ሰዎችም ቦታ ቦታ ይዘው በተፈለገው ጊዜ አድርጉ የተባሉትን ለማድረግ የታቀደው በከፊል ተሳክቶለት ነበር:: የቃሊቲው እስር ቤት ድራማ፤ ከአሜሪካ አምባሳደር ቪኪ ሀደልሰን ጋር የነበረው ዱለታና በውጭ ያስቀመጣቸው እነ አንዳርጋቸው ጽጌ፤ ብርሃነ መዋ፤ ዳንኤል አሰፋ፣ ዶክተር ሞገስ ገብረማርያም የሰጣቸውን የውጭውን ትግል በማፈራረስና ተለጣፊ በማፍራት በአሳሳችና አጣዳፊ ሁኔታ በትግሉ ላይ ብዙ ጥፋት ሲያደርሱ አይተናል::

ወያኔ የቅንጅት መሪዎችን ከእስር ቤት ለመፍታት የቻለበት አንደኛው ምክንያት ከቃሊቲ ቢወጡም በቂ የመከፋፈል ሥራ ስለተሰራ ቅንጅት አያንሰራራም የሚል ግምት ስላለውና በነብርሃኑ ነጋ የውስጥ ስራ በመተማመን ነበር:: አዎን ብዙው ደጋፊ ግራ ተጋብቶ፣ ተበሳጭቶ፣ አንገቱን ደፍቶ፣ አቋሙን ቀይሮ ለትግሉ መጓተት በየቦታው ትንሽ ትንሽ አስተዋጽኦ አድርጓል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በጠራ አቋሙ ጽናቱና እምነቱ እንዳለ ነው::

ዋናው መሰሪ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ካድሬዎቹና ተከታዮቹ ትግሉን ተቆጣጥረናል አዳክመናል ብለው ሲዝናኑ እና ጉሩ ወሸባዬ ሲሉ እውነት ግን ተደብቃ አትቀርምና እውነቱ ስትወጣ፣ የእርሱንና ካድሬዎቹን ተንኮልና ሴራ ሕዝብ እያወቀው ሲመጣ በገጠማቸው የፓለቲካ ኪሳራ የግዴታ ዘዴያቸውን በየጊዜው መቀያየር ነበረባቸው:: ዶክተር ብርሃኑ እና አቶ አንዳርጋቸው አንዴ "ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ"፣ ሌላ ጊዜ ዲሞክራቲክ አሰራር፣ ሲያሰኛቸው ከሰላማዊ ትግል ወደ መሳሪያ ትግል እየቀያየሩ፣ አንዴ ቅንጅት ነን ሌላ ጊዜ ከቅንጅት ወጥተናል በማለት የሚይዝ የሚጨብጠ-ትን አጥተዋል:: ዶክተር ብርሃኑ ከአሻንጉሊቱ ወይዘሮ ብርቱካን ጋር ተለያይተናል ሲሉ እርሷ ደግሞ የማውቀው ነገር የለም ስትልና የእራሷን ፓርቲ ስትመሰርት ቆይታለች:: ዞሮ ዞሮ የተለያዩ ይምሰሉ እንጂ አንድ ናቸው:: ዓላማቸው ያው የወያኔን ዓላማ መፈጸም ነው:: ይኸውም ቅንጅትን ማፈራረስ ነው:: አልተሳካላቸውም:: አይሳካላቸውምም:: በቅርቡ እንኳን ብርሃኑ ነጋ በቅንጅት ስም ካናዳ ውስጥ ስብሰባ ባደረገ በሶስተኛው ቀን ከቅንጅት ወጥተናል እንዳላለ፣ ከሁለት ሳምንት በፊት ደግሞ "ግም ሞት 7" የሚሉት ድርጅት መስርተናል እንዳላለ ሁሉ ዛሬ ደግሞ ጁን 8 ቀን በቅንጅት ስምና አርማ በተጠራ ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ለንደን ያለው የአንዳርጋቸው ቡድን በቅንጅት ስም ማስታወቂያ አውጥቷል:: ዶክተር ብርሃኑ ምናልባት ከምሽት እስከ ውድቅ ለሊት ድረስ ከመለኪያ ጋር መታየቱና ማዘውተሩ የአእምሮ ጤና ማጣት ችግር ውስጥ አስገብቶት እንዳይሆን ወዳጅ ነን የሚሉት ወደ የአዕምሮ ሀኪም ዘንድ ቢወስዱት ሳይሻል አይቀርም:: ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽና ይሁንታ ያገኘ ፓርቲ እንጂ ጥቂት የወያኔን እድሜ ለማራዘምና የራሳቸውን የተመቻቸ ሕይወት ለማስተካካል የሚሯሯጡ ግለሰቦች የፈጠሩትና የሚያፈርሱት አይደለም::

እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ አሁን ደግሞ ሌላ ጨዋታ አምጥተዋል:: የእነርሱን ብጤ ደጋፊዎች እያሰባሰቡ ነው:: ከኢሕአፓ የተገነጠለውን አንጃ ቡድን ይዘው ወደ ወያኔ ለመግባት ማመልከቻ አስገብተው ደፋ ቀና እያሉ ነው:: መለስ እንኳን ሞኝ አይደለም እነርሱን እሺ አሰኝቶ ማመልከቻቸውን ለማስረጃ ይዞ እያስፈራራ ነገ አድርጉ የሚላቸውን እንዲያደርጉ እያመቻቻቸው

ነው። ሆኖም ግን በዚህ ወዶ ገባና ታማኝ ተቃዋሚ ለመሆን የሚያደርጉትን ሩጫ ሕዝብ በማወቁና ተቃውሞ ስለበዛባቸው ይህንን አንጃ ቡድን በአዲስ ኃይልና በተለየ ፊት ወደፊት እንዲገፋ ተነጋግረው ሰሞኑን ውር ውር ሲሉ ይታያሉ። እነ ብርሃኑ ነጋና አቶ መርሻ ዮሴፍ አንድ ላይ መሆናቸውን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች እየታዩ ነው። እነ ብርሃኑ ነጋ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን አምባገነን ናቸው በማለት ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሂደው የውጭውን ደጋፊ ግራ እንዳጋቡት ሁሉ በአንጻሩ እነ አቶ መርሻ ዮሴፍ ደግሞ አቶ እያሱ ዓለማየሁን አምባገነን ናቸው ሲሉ የስም ማጥፋት ዘመቻ መክፈታቸው አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር ሲሆን፤ የአንጃው ቡድን አባላት የብርሃኑ ነጋን የሚዲያ መድረኮች እየተጠቀሙ በከረንት አፌርስ ድምጻቸውን ማሰማታቸው፤ ማስታወቂያ በነብርሃኑ ሚዲያ በኩል ማውጣታቸው በቅርብ እንደሚሰሩ ያሳያል። አሁን ማቆም ያቃታቸው ይኸው ስራቸው ታውቆ በየቦታው ስለሚታወቁ ያንን ሽፋፍኖና ካባ ደርበው የሚያልፉበትን መንገድ እየፈለጉ ነው። በቅርቡ ደግሞ "መሰዳደብ ይቁም፣ መጣላት ይቅር" በሚል ፈሊጥ እነርሱ ከዓመት በላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሂደው ትግሉን ካዳከሙና ደጋፊውን ከከፋፈሉ በኋላ የብርሃኑ ነጋ መጋለጥ አንዲት እርምጃ እንዳይራመዱ ስላደረጋቸው "በአንድነት" እንስራ ስም ዝም በሉ አትሳደቡ ብርሃኑም ከተራራ ላይ ሆኖ ይቀልድ መርሻም ወደ ወያኔ ይግባ ዝም በሉ ማለት ይዘዋል። ባንዳ እና አንጃ ግምባር ፈጥረው እነሰዬ አብርሃን ይዘው ከሌሎች ከሃዲዎች ጋርም ግምባር ፈጥረው ለ2010 የወያኔ ምርጫ አጫፋሪ ለመሆን እየተዘጋጁ ስለሆነ ያንን ሕዝብ አውቆ እንዳይከላከላቸው መንገድ ለመዝጋት ነው። የተቃዋሚውን ድምጽ ለመዝጋት ነው። የአንድነት ኃይሉን ትግል ለመንጠቅ ነው።አንዴ መታለል መሳሳት ያለ ቢሆንም በእነዚህ የሕዝብ አመኔታ በሌላቸው ወዶ ገብ ባንዳ እና አንጃ ከአሁን በኋላ የሚታለል እንደሌለ ተገንዝበው የአንድነት ኃይሉ ክፍል ግራ ከማጋበት እንዲቆጠብ እናሳስባለን።

እነ ዶክተር ጌታቸው በጋሻው ከወያኔው ክንፈ ጋር አታዋ ላይ ባለፈው ዓመት ያደረጉት ስብሰባ ለዛሬው ጉዞአቸው ጥርጊያ መንገድ መሆኑ እየታየ ነው። አሁን ደግሞ ተዉን እባካችሁ አንጃ ና ባንዳ አትበሉን ይሉናል። እንደዚያ ያሰኛቸው ስራቸውና ተግባራቸው ነው። አሁንም ቢሆን እነዚህ ባንዳ እና አንጃ ቡድኖች በየሄዱበት ተቃውሞ እንደሚገጥማቸው ሊያውቁት ይገባል።

"እነ ኢንጂነር ኃይሉ አገር ቤት ሊመለሱ ነው" "እኛም አገር ቤት ገብተን እንታገል ነው የምንለው እና የእኛ መግባታችን ለምን አዲስ ነገር ይሆናል?" ይላሉ የኢሕአፓ አንጃዎች። ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል አሉ አበው። ኢንጂነር ኃይሉ የሕዝብ ኃላፊነትና የፓርቲ መሪ ስለሆኑ የጀመሩትን ትግል በቆራጥነት ለመቀጠል ከወያኔ ጋር ሊፋለሙ በውጭ አገር የሚያደርጉትን ሕክምና ሲጨርሱ ሄደዋል። እሳቸው ለውጥ ለማምጣት እንጂ ሥልጣን ለመካፈልና ታማኝ ተቃዋሚ ሊሆኑ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃቸዋል ያከብራቸዋል እሳቸውም ያውቁታል ያከብሩታል። እነ አቶ መርሻ እና ዶክተር ጌታቸው በጋሻው የሚሉን ለምርጫ 2010 ለመድረስ ዛሬ ወያኔ ጋር ገብተን መስራት አለብን ነው። ተቃዋሚዎች እነ ልደቱ፣ ብርቱካን፣ አየለ ጫሚሶ፣ በየነ ጴጥሮስ ወዘተ.... አሉ እኛስ ምን ይጎድለናል ነው አባባላቸው። እነ ዶክተር ጌታቸው በጋሻው የቅንጅትን መሪ የኢንጂነር ኃይሉን ስም ከ2004 ዓም ጀምሮ ሲያጠፉና ትግላቸውን ሲያንኳስሱ እራሳቸውን በማንዴላ ቦታ አስገብተው ኢንጂነር ኃይሉን ለነጮች ባደረው ባንዳ ቦታ ሲያስቀምጡና በየኢንተርኔቱ ጽፈው መበተናቸውን አንዘነጋውም ፣ ከምርጫው በኃላ ታስረው አንድም ቀን በተቃውሞ ሰልፍ ላይ ይፈቱ ሳይሉ፣ እነ አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ በቅንጅት ላይ ያን ያህል ጥፋት ሲያደርሱ ከመደገፍና አብረዋቸው ውር ውር ከማለት በቀር ላለፉት ሶስት ዓመታት ምን ሰሩ? እስቲ ይህን ስናደርግ ከረምን ይበሉ ታዲያ ዛሬ የትግሉ መሪ ለመሆን ዘጥ ዘጡ ለምንድነው? የእነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እና አቶ መርሻ ዮሴፍ በየከተማው የሚያደርጉት ሥራ የተቃዋሚውን ጎራ መከፋፈልና ማዳከም ግራ ማጋባትና መበተን ነው። ይህንን አውቆ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። ካናዳ ቶሮንቶ ያሉት ጀግኖቻችን በባንዳው ክፍል ላይ ያሳዩት አቂም ጥሩ አርአያ ነው። በለንደንም ሌላም ቦታ መቀጠል አለበት።

አዬ ሆዳምነት አዬ ሥልጣን መውደድ አዬ በሕዝብ ትግል መቀለድ። አገር ቤት ታማኝ ተቃዋሚ ለመሆንማ የእነ ዶክተር በየነ ጴጥሮስ፣ የልደቱ እና ብርቱካን ክህደት አይበቃንም? ኸረ በህግ አምላክ አደብ ግዙ። ምን ለምን አብረሀ አዝግም ነው የተባለው?

ሜይ 31 2008